IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

# AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2
# AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2
# AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2

Friday 23 May 2003 (afternoon)
Vendredi 23 mai 2003 (après-midi)
Viernes 23 de mayo de 2003 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

## INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works, will not score high marks.

## INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Traiter un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3$^{e}$ partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2$^{e}$ partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3$^{e}$ partie n'obtiendront pas une note élevée.

## INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

**ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ መጠነኛ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: ይህ ግን በክፍል 3 ስር ከሚገኙት ቢያንስ ሁለት ስራዎች በተጨማሪነት ብቻ መሆን አለበት:: ሌሎች ስራዎችን ማጣቀስም ይቻላል:: ሆኖም የመልስህ(ሽ) አቢይ ክፍል ሌሎቹ ስራዎች ላይ መመስረት የለበትም::**

**ድራማ**

**1.** ተከታዩን

(ሀ) ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ሀያል የሆነው ሀይል ከሌለው ጋር ያለውን ግንኙነት በንጽጽር ግለጥ ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ዋናው ገፀባህሪ እንዴት እንደቀረበ ለማሳየት ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመውሰድ አነፃጽር:: የቀረበበት መንገድ ገፀባህሪውን ለመረዳትና ሚናውን ለማወቅ ያደረገውን አስተዋጽኦ አብራራ::

**ረጅም ልቦለድ**

**2.** ተከታዩን

(ሀ) በልቦለድ ሴራና ገፀባህርያት መከከል ያለውን ግንኙነት ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማስደገፍ ደራሲያን ፍትህን እና ፍትህ አልበኝነትን እንደምን እንዳቀረብዋቸው አነፃጽር::

**ስነግጥም**

**3.** ተከታዩን

(ሀ) ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ሶስት ግጥሞች በመጥቀስ ተፈጥሮ እንደምን እንደቀረበና ተፈጥሮ በግጥሞቹ ውስጥ ያለውን ሚና አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) በስነግጥም ውስጥ ምስል ፈጠራ የሚጫወተውን ሚና ያነበብካቸውን ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ::

**ስድንባብ**

**4. ተከታዩን**

(ሀ) አንድ ስድ ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) ዋነኛ መለያው አንባቢውን ማሳመን መቻሉ ነው። ይህንን ሃሳብ አብራራ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) ገለፃና ምልልስ ከአጭር ልቦለድና ከረጅም ልቦለድ ውጪ ባሉ ስድ ጽሁፎች (ለምሳሌም ወግ) ውስጥ ቁልፍ ሚና አላቸው። ይህንን ሃሳብ ግለጽ።

**አጭር ልቦለድ**

**5. ተከታዩን**

(ሀ) ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሶስት አጭር ልቦለዶች በመጥቀስ መነሻ ምእራፎች እጅግ ጠቃሚ መሆናቸውን አስረዳ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) የተዋጣለት አጭር ልቦለድ አሳሳል ተአማኒነትንና ግለወጥነትን ይጠይቃል። ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን አጭር ልቦለዶች በመመርኮዝ ግለጽ።

**6. ሁለገብ(አጠቃላይ)**

ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)።

(ሀ) ስነጽሁፍ ከአንድ በላይ ትርጉም የያዘ ጽሁፍ ነው። ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት አስረዳ። ደራስያን ለአንባብያን ሃሳባቸውን የሚገልጹባቸውን መንገዶች አነፃጽር።

ወይም

(ለ) ስራቸውን ያጠናህላቸው ደራስያን ተምሳሌትንና ምስል ፈጠራን ምን ያህል ተጠቅመዋል? የተጠቀሙትስ ለምንድነው? መልስህ ቢያንስ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚያወዳድር ይሁን።

ወይም

(ሐ) ባጠናሃቸው ሁለት ስራዎች የሚገኘው አስቂኝ ሁኔታ ምንጩ ምንድነው? የአስቂኙ አቀራረብ አላማስ ምን ይሆን?

ወይም

(መ) ስነጽሁፍ መነሻውና ዋነኛ መለያው የፈጠራ ውበቱ ቢሆንም በስነጽሁፍ ከረር ያሉ ቁምነገሮችም ይቀርባሉ። ይህንን ሃሳብ በምሳሌ አብራራ።

---